# የትምህርት ዓመት 2019/2020 የምዝገባ ማጠናቀሪያ

እንኳን ለዲስ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለ 2019/2020 ለዲሲ የትምህር ዓመት በደህና መጡ! እባክዎን ለመጭው 2019-2020 የትምህርት ዓመት ይህንን የምዝገባ ማጠናቀሪያ ቅጽ ይሙሉ። የእያንዳንዱን ቅጽ መልሶችዎን ታይፕ ማድረግ እንዲችሉ ሊሞላ በሚችል ፒዲኤፍ (PDFs) እና የሚያስፈልጉ ነጥቦች ገና ታይፕ ማድረግ ሲጀመር ጽሁፉ ዝርግፍ ብሎ በማጠናቀሪያው ላይ በሙሉ እንዲመጣ (pre-populate throughout the packet) አድርገን አቅርበናል።

ሲጨርሱ፣ በማጠናቀሪያው ላይ ያለውን ያትሙ፣ የድጋፍ መርጃዎቻችዎን ይሰብስቡ፣ እና ወደ ትምህርት ቤትዎ ጽሕፈት ቤት ወስደው ያስረክቡ። ከዚህ በታች ደረጃ በደረጃ መመሪያዎች ተዘርዝረዋል። መረጃዎችን ሁሉ በ http://enrolldcps.dc.gov/ ላይን ላይ ያገኟቸዋል። ትርጉሞችም በአማርኛ፣ በቻይኒስ፣ በፈረንሣይኛ፣ በስፓኒሽ እና በቪየትናም ቋንቋዎች ይገኛሉ። በዲሲፒኤስ፣ የተማሪን መረጃ ለፌድራላዊው መንግሥት አንሰጥም።

ተማሪዎቻችን ከዚህ በፊት ያለፉባቸው ቀደም ያሉ ሁኔታዎቻችውም ሆኑ ወይንም አሁን የሚገኙባቸው ሁኔታዎቻቸው የፈለገውን ዐይነት ቢሆኑም፣ በዲሲፒኤስ ተልእኮ አችን፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤታችን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቦታውን የጠበቀ፣ ተቀዳሚነትና ጥራት ያለው፣ ተማሪዎቻችን ሁሉ ለኮሌጅ፣ ለሙያ፣ እና ለሕይወት የሚያዘጋጅ ትምህርት ለማቅረብ ነው። ተማሪዎችን ሁሉ ለማገልገል ክብር እና ኃላፊነት ሲሆን፣ ሌላ ግሩም መጪ የትምህርት ዓመት እየጠበቅን ነው።

## እርምጃ 1. በዚህ ይዘት ውስጥ ያሉትን ቅጾች ይሙሉ

ሀ. መመዝገቢያ ቅጽ
ለ. የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ
ለ. የስምምነት መግለጫ ቅጾች (ለብዙኃን መገናኛ አገልግሎቶች እዲጠቀሙባቸው ስምምንት መግለጫ፣ ለውትድርና መልማዮች፣ እና ማኅበራዊ ስሜትዊ የጤና አግልግሎቶች መረጃዎች እንዲሰጡ መፍቀድ)
ሐ. ትምህርት ቤቴ ዲሲ በትምህርት ቤት ቦታ መቀበል *(የሚቻል ከሆነ)*
መ. የተማሪ እና የወላጅ/የአሳዳጊ መብቶች ማስታወቂያዎች
ሰ. የምግብ ማመቻቻ ቅጽ *(የሚቻል ከሆነ))*
ረ. መሟላት ያለባቸው ክትባቶች
ሠ. የዜጋዎች ሁሉ የጤና ጥበቃ ቅጽ
ሸ. የአፍ ውስጥ ጤንነት ቅጽ
ቀ. የመድኃኒት እቅድ/የአወሳሰድ ቅጽ *(የሚቻል ከሆነ))*

## እርምጃ 2. የድጋፍ መረጃዎችዎን ማሰባሰብ

*ተማሪዎን ለማስመዝገብ ጥቂት የድጋፍ መረጃዎች ብቻ ነው የሚያስፈጉ።*

**ለማናቸውም ዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት አዲስ**

ሀ. አንድ የኣድሜ ማረጋገጫ – ምሳሌዎች የልደት ምስክር ወረቀት፣ የሀኪም ቤት ወረቀቶች፣ የበፊት ትምህርት ቤት ማስረጃዎች፣ ፓስፖርት፣ ወይንም የጥምቀት የምስክር ወረቀት ማስረጃዎችን ጭምር ያጠቃልላል።
ለ. የነዋሪነት ማረጋገጫ – ተቀባይነት ያላቸውን የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ እና የተሟሉ ዝርዝሮች እና የማረጋገጫ መንገዶች

**ተማሪው አሁን ወደሚማርበት ዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቱ መመልሰ**

- የነዋሪነት ማረጋገጫ – ተቀባይነት ያላቸውን የተሟሉ መረጃዎች ቅጽ ዝርዝር እና የማረጋገጫ ዘዴዎች ለማየት የነዋሪነት ቅጹን ይመልከቱ።

## እርምጃ 3. ለልጅዎ ትምህርት ቤት ጽሕፈት ቤት የድጋፍ ጥንቅሮቹን እና ማስረጃዎችዎን ሁሉ ያስረክቡ።

የመመዝገቢያ ሠነዶች ለተማሪ ልጅዎ 2019/2020 ትምህርት ቤት በመሠረቱ በሥራ ሰዓት ነው መቅረብ ያለባቸው።

## እርምጃ 4. የነጻ ምሳ ማመልከቻውን ለመሙላት በቀን መቁጠሪያዎ ላይ ማስታወሻ ይያዙ።

ልጅ ምሳ በነጻ እንዲሰጠው የቤተሰብ ማመልከቻ ሀምሌ (July) 2019 ይገኛል። ማመልከቻዎቹ ለቤተሰብ ኢሜይል ይደረጋሉ። ቤተሰቦች ሁሉ ማመልከቻ እንዲያስገቡ ይበረታታሉ።

*ልጆቹን ለማስመዝገብ የሚፈልግ እያንዳንዱ ወላጅ፣ ዲሲፒኤስ፣ የዲስትሪክት ነዋሪነቱን በየዓመቱ እንዲያረጋግጥ ህግ ይጠይቃል። በም ዝገባ ሰዓት ዲሲፒኤስ ይህንን የነዋሪነት ማረጋገጫ (የዲሲነዋሪነት ማረጋገጫ ተማሪው ለመጀመሪያ ጊዜ ለመመዝገብ በሚፈልግበት ሰዓት በዐሥር የትምህርት ቀናት ውስጥ መረጋገጥ አለበት። ዲስትሪክቱ እንዲሟላ በሚጠይቀው መሠረት የዲስትሪክት ነዋሪነትዎን ማረጋገጥ ካልቻሉ፣ ወይንም የዲስትሪክት ነዋሪ ያልሆነ የሚጠየቀውን ክፍያ ለመክፈል ካልተስማሙ፣ ተማሪዎ በዲሲፒኣስ ትምህርት ቤቶች ከመማር የመታገድ ወይንም የመገለል እድል ሊያጋጥመው ይችላል። ለበለጠ መረጃ እባክዎን የዲሲፒኤስ የምዝገባ ቡድንን በ enroll@k12.dc.gov ላይ ይቃኙ ወይንም 202-478-5738 ደውለው ያነጋግሩ።*

***መድልዎ አልባ ማስታወቂያ፤*** *በስቴት እና በፌድራላዊ ህገ ደንብ መሠረት፣ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ በእውን ወይንም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ወይንም በሚታሰብ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ ትዳር በመያዝም ሆነ ባለመያዝ፣ በመልክ፣ ለማፍቀር በሚፈልጉት የጾታ መደብ ዝንባሌ ምርጫ (sexual orientation)፣ ለመሆን በሚፈለግ የጾታ መደብ ወይንም የጾታዊነት ፍላጎት መገለጫ፣ (gender identity or expression)፣ በቤተሰብ የዝምድና አቋም (family status)፣ በቤተሰብ ኃላፊነት፣ በትምህርት ደረጃ፣ በፖለቲካ ዝንባሌ፣ በ ጄኔቲክ መረጃ, (genetic information)፣ በአንዳች እክል ምክንያት፣ በገቢ መንጭ፣ በቤተሰብ አባላት መካከል በሚፈጠር የእርስ በእርስ ግጭት ተጠቂ በመሆን፣ ወይንም በሚኖሩበት ቦታ ወይንም በሚሠሩት የሥራ ዐይነት የተነሣ፣ መድልዎ አያደርግም። ስለዚህ ጽሑፍ እና ተጨማሪ መረጃም ለማግኘት http://dcps.dc.gov/non-discrimination. ይቃኙ።*

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# የትምህርት ዓመት 2019/2020 የመመዝገቢያ ቅጽ

ወደ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት የሚመለሱ እያንዳንዱ ተማሪዎን ለማስመዝገብ **በዚህ ቅጽ ይጠቀሙ።** ለ 2019/2020 የትምህርት ዓመት ተማሪዎ ለሚማርበት ትምህርት ቤት፡ ይህንን ቅጽ ወስደው በአካል ያስረክቡ። ከዝህ በታች ያሉት ጥያቄዎች ሁሉ መመለስ አለባቸው,።

## የዲሲፒኤስ ተማሪ፤

| | | |
|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ስም፤** | **የመጨረሻ ስም፤** | **የትውልድ ዘመን፤** |

**የትውልድ ሀገር፤** | **ጾታ፥** ☐ ወንድ ☐ ሴት ☐ ከሁለቱም ያልሆነ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **የቤት አድራሻ፤** | **አፓርትማ፤** | **ከተማ፤** | **ስቴት፤** | **ዚፕ፤** |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የትምህርት ዓመት 2018/2019** | **የትምህርት ቤት ስም፤** | **ከተማ፥** | **ስቴት፤** |
| **የትምህርት ዓመት 2018/2019** | **የትምህርት ቤት ስም፤** | | |

**ለትምህርት ዓመቱ የክፍል ደረጃ 2019/2020:** *አንዱ ላይ ያመልክቱ*
☐ Pre-K3 ☐ Pre-K4 ☐ *መዋዕለ ሕጻናት* ☐ 1st ☐ 2nd ☐ 3rd ☐ 4th ☐ 5th
☐ 6th ☐ 7th ☐ 8th ☐ 9th ☐ 10th ☐ 11th ☐ 12th ☐ የጎልማሶች ትምህርት

የስደተኛነት ደረጃ፤ በአለፉት 36 ወራት ውስጥ ተማሪው፣ ልጃቸው፣ ባለቤት፣ ወላጅ ወይንም አሳዳጊ ሞግዚት ስደተኞች ከሚሠ ሯቸው ሥራዎች ጋር የተዛመዱ (ማለትም ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ ከግብርና ወይንም ዓሣ ማጥመድ ከመሳሰሉ) ወቅታዊ ሥራዎች ሠርቷል)? ☐ የለም ☐ አዎን

**የቤት ሁኔታ** አንዱ ላይ ብቻ ምልክት ይድርጉ ☐ ቋሚ (የራስ፣ የኪራይ) ☐ ሆቴል/ሞቴል ☐ *መጠለያ* ☐ *መጠለያ የሌለው* ☐ ብቻውን የመጣ ወጣት ☐ ማደጎ እንክብካቤ/CFSA ☐ አሳዳጊ የሚጠብቅ ☐ ደባል

**የዘርያ ምድብ፤** *አንዱ ላይ ብቻ ምልክት ይደረግ* ☐ ስፓኒሽ/ላቲኖ ☐ ስፓኒሽ ያልሆነ/ላቲኖ ያልሆነ

**ዘር፤** *በሚመለከተው ላይ ብቻ ምልክት ያድርጉ* ☐ አሜሪካዊ ህንድ/የአላስካ ተውላጅ ☐ ኤሽያዊ ☐ ተወላጅ ሀዋያን/ የፓሲፊክ ደሴት ተወላጅ ☐ ጥቁር/አፍሪካዊ አሜሪካዊ ☐ ነጭ

**ተማሪው ከሚከተሉት አንዱ ይኖረዋል?** *በሚመለከተው ላይ ብቻ ምልክት ያድርጉ። ምልክት የተደረገበትን ትምህርት ቤት ሊከታተል ይችላል።* ☐ 504 እቅድ ☐ መድህኒት የሚያስፈልገ ☐ IEP ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ☐ አለርጂ ☐ የተወሰነ ምግብ የሚያስፈልገው

## ወላጅ/አሳዳጊ/ጠባቂ/ተንከባካቢ

ተንከባካቢ አንድ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ስም፤** | **የመጨረሻ ስም፤** | **ለተማሪው ያለ ዝምድና፤** | | |
| **ኢሜይል፤** | **ስልክ፤** ☐ ሴል ☐ የቤት ስልክ | | | |
| ☐ ከተማሪው ጋር አንድ ዐይነት **አድራሻ፤** | **አፓርትማ፤** | **ከተማ፤** | **ስቴት፤** | **ዚፕ፤** |

☐ ስለ ተማሪየ አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት በኤሜይል/በቴክስት እንዲደርሰኝ አልፈልግም።

ተንከባካቢ ሁለት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ስም፤** | **የመጨረሻ ስም፤** | **ለተማሪው ያለው ዝምድና፤** | | |
| **ኢሜይል፤** | **ከተማ፤** ☐ ሴል ☐ የቤት ስልክ | | | |
| ☐ ከተማሪው ጋር አንድ ዐይነት **አድራሻ፤** | **አፓርትማ፤** | **ከተማ፤** | **ስቴት፤** | **ዚፕ፤** |

☐ ስለ ተማሪየ አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት በኤሜይል/በቴክስት እንዲደርሰኝ አልፈልግም።

## በቤት ስለሚነገር ቋንቋ አሰሳ መጥይቅ። *በቤት ስለሚነገር ቋንቋ ለሚጠየቁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች የሚሰጡ መልሶች የሚያመለክቱት ከእንጊሊዘኛ ሌላ ወይንም ተጨማሪ ቋንቋ የሚነገር መሆኑን የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አገልግሎቶች የሚሰጡ መሆናቸውን እርግጠኛ ለማድረግ የተማሪው የእንጊሊዘኛ ቋንቋ የቅልጥፍና ደረጃ ይመዘናል። ለጥያቄዎች፣ እባክዎን ለቋንቋ ትምህርት ዋና ክፍል (Language Acquisition Division) 202-671-0750 ደውለው ያነጋግሩ።*

**ከበቤት ከእንጊሊዝኛ በስቀቀር ሌላ የሚነገር ቋንቋ አለ ወይ?** ☐ የለም ☐ አዎን፤ ____________________ *(ቋንቋውን ይግለጹ)*

**ልጅዎ ከቤት ከእንጊሊዘኛ ሌላ የሚግባባበት ቋንቋ አለው ወይ?** ☐ የለም ☐ አዎን፤ ____________________ (ቋንቋውን ይግለጹ)

**ከትምህርት ቤት በምን ቋንቋ ነው መረጃ እንዲደርስዎ የሚፈልጉት?** *"ሌላ" የሚል የተመረጠ ከሆነ፣ የጽሁፍ መላላክ በእንጊሊዘኛ ይካሄዳል። አስተርጓሚ ሲገኝ ይላካል።* ☐ እንጊሊዘኛ ☐ ስፓኒሽ ☐ አማርኛ ☐ ፈረንሣይኛ ☐ ቻይንስ ☐ ቪየትናሚስ ☐ ሊለ፤________________

## ለድንገተኛ ጊዜ መገናኛ *ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱን ዐዋቂዎች ማግኘት የማይቻል ከሆነ ልጅዎን ከትምህርት ቤት ተቀብሎ ወደ ቤቱ የሚያደርሰው ማን ነው ?*

| | | |
|---|---|---|
| **ሙሉ ስም፤** | **ለተማሪው ያለው ዝምድና፤** | **ስልክ፤** |
| **ሙሉ ስም፤** | **ለተማሪው ያለው ዝምድና፤** | **ስልክ፤** |

## በዲሲፒኤስ የተማሪው ወንድም እህት። *በዲሲ ፒኤስ ትምህርት ቤት ስለሚማሩ ወንድም እህት ተማሪዎች ሁሉ እባክዎን መረጃዎች ይስጠ፤*

| | ወንድም እህት 1 | ወንድም እህት 2 | ወንድም እህት 3 | ወንድም እህት 4 |
|---|---|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ስም፤** | | | | |
| **የትውልድ ዘመን፤** | | | | |

## ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው ማረጋገጫ

ከላይ የቀረበው መረጃ በሙሉ እስከማውቀው ድረስ ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ። ዲሲፒኤስ ይህንን መረጃ በምስጢር በመጠበቅ ለዲሲፒኤስ አገልግሎት ተግባር ብቻ እንደሚጠቀምበት እረዳለሁ። የተሳሳተ መረጃ መስጠት በህግ እንደሚያስቀጣ ዐውቃለሁ።

**ስምዎን በጉልህ ይጻፉ፤** ______________________________ **ፊርማ፤** ______________________________ **ቀን፤** ___________

**የዲስትሪክቱ ነዋሪ መሆንዎን** ለማረጋገጥ ይሄንን ቅጽ ይጠቀሙ እና በዚህም የተነሳ እርስዎ እና የእርስዎ ተማሪ ልጅ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት ወይም የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ ለመግባት ብቁ ትሆናላችሁ።

## ቅደም ተከተል አንድ፦ በተሻለ ሁኔታ የሚመጥኖትን የማረጋገጫ ዘዴ ይምረጡ።

የዲሲ ነዋሪነትዎትን ለማረጋገጥ የሚስችሉትን ሁሉንም ዘዴዎች ዝርዝር ገጽ ሁለት ላይ ይገኛሉ። **ከታች** 2 እና 3 ክፍልን ካጠናቀቁ በኋላ አንድ ይምረጡ። የዲሲ የሕዝብ ወይም የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ የምዝገባ መስፈርት ለማሟላት፡ 1)ልጁን የሚያስመዘግበው ግለሰብ አግባብ የሆነ ሰነድ ያለው ወላጅ፣ ትክክለኛ የሕግ ሞግዚት፣ ጠባቂ ወይም ሌላ ቀዳሚ ተንከባካቢ መሆን አለበት፣ 2) ግለሰቡ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ በአካል የኖረ መሆን አለበት፣ እና 3) በሕግ እና ደንቦች ላይ እንደተቀመጡት የነዋሪነትን የሚያረጋግጡ ትክክለኛ እና አግባብ ያላቸው ሰነዶች ማቅረብ አለበት።

## ቅደም ተከተል ሁለት፦ ስለ ቤተሰብዎ መረጃ ያቅርቡ።

| **የተማሪው/ዋ የመጀመሪያ ስም፦** | **የተማሪው/ዋ የአያት ስም፦** | **የትውልድ ቀን፦** |
|---|---|---|

| **የ SY18/19 ትምህርት ቤት ስም፦** | **የ SY19/20 ትምህርት ቤት ስም፦** |
|---|---|

| **ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ > መጀመሪያ ስም፦** | **የአያት ስም፦** |
|---|---|

**እኔ የሚከተለው ነኝ፦**
- ❑ አዋቂ ተማሪ
- ❑ ታዳጊ ተማሪ እና የቃለ መሃላውን መግለጫ ሞልቼአለሁኝ
- ❑ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ/ጠባቂ
- ❑ የተማሪው ሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ እና የ OPC ቅጽን ሞልቼአለሁኝ

**ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ አድራሻ፦**

| **ከተማ፡** | **ግዛት፡** | **ዚፕ፦** | **ኢሜይል:** | **ስልክ፦** |
|---|---|---|---|---|

## ቅደም ተከተል ሦስት፦ የነዋሪነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

- እኔ ወላጅ ወይም ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ጠባቂ፣ ወይም ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ እንደሆንኩኝ አረጋግጣለሁኝ እና በዚህም መሰረት ሕጋዊ እና ተገቢ ሰነድ እያቀረብኩኝ ነው፦
- እኔ "ለተከታታይ ጊዜ ያህል ለመኖር ፍላጎቱ የሚያሳይ የመኖሪያ ቤት መያዝ እና መኖር" በመባል የሚገለጸውን በዲስትሪክቱ ውስጥ በአካል በመገኘት መኖር እንደጀመርኩኝ እና እንደምኖር አረጋግጣለሁኝ፣ እና በ 5-A DCMR § 5004 ላይ እንደተቀመጠው፣ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ ሕጋዊ እና ተገቢውን ሰነድ እያስረከብኩኝ ነው።
- እኔ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ፈንድ በሚደረጉት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ ወይም የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ከላይ የተጠቀሰውን ተማሪ ማስመዝገብ በአካል በመገኘት የሚሰጠውን የቃለ መሃላ መግለጫ ጨምሮ የዲሲ ነዋሪነትጥሩ **እምነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እና ነዋሪነትን የሚያረጋግጡ ሕጋዊ እና ተገቢ ሰነዶችን በማቅረቤ እንደሆነ ተረድቼአለሁኝ።**
- ምንም እንኳን በእኔ የቀረቡት ሰነዶች አጥጋቢ ቢሆኑም፣ OSSE ወይም የትምህርት ቤቱ ሃላፊዎች፣ ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ፣ የተማሪውን ነዋሪነት ወይም ተማሪውን የሚያስመዘግበው አዋቂ ግለሰብ የሌላ ቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ አቋምን ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃዎችን ሊጠይቅ ይችላል።
- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ፣ በግዛቱ የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education) በኩል፣ ነዋሪ እንዳልሆንኩኝ በሚወስንበት ሰዓት፣ ለተማሪው የትምህርት ተመላሽ ክፍያ ለመክፈል ባለዕዳ እንደሆንኩኝ፣ እና ተማሪው ከትምህርት ቤት ሊወጣ እንደሚችል ተረድቼአለሁኝ።
- የሐሰት መረጃ ወይም ሰነድ ያቀረብኩኝ እንደሆነ፣ ለዲሲ የወንጀል ምርመራ አጠቃላይ ምርመራ ቢሮ (DC Office of the Inspector General for criminal prosecution) ልወሰድ እንደምችል ወይም ለዲሲ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ (DC Office of the Attorney General) በኩል ከተማሪ ነዋሪነት ማረጋገጫ ጋር በተያያዘ ለመንግስት ሠራተኛ የሐሰት መረጃ ሆን ብሎ በማወቅ የሚሰጥ ማንኛውም ግለሰብ ከ$2000 ዶላር ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ወይም ከ90 ቀናት ያልበለጠ እስር እንደሚቀጣ፣ ነገርን የገንዘብ ቅጣት እና እርስ ሁለቱም በአንድ ጊዜ አይተገበሩም የሚለው የዲሲ ኮድ § 38-312 ስር የሚገኘው የሐሰት ይገባኛል ጥያቄ ሕግ መሰረት ክስ ሊመሰረትብኝ እንደሚችል ተረድቼአለሁኝ።
- ከዚህ ቅጽ ጋር የሚያያዙት ሁሉም ሰነዶች በትምህርት ቤት እንደሚያዙ እና የ OSSE፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና በሚጠየቅበት ሰዓት፣ የዲሲ ጠቅላይ መምሪያ ቢሮ እና ለዲሲ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ ጨምሮ ለሌሎች ኤጀንሲዎች ተላልፈው እንደሚሰጡ ተረድቼአለሁኝ።
- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የእኔን ነዋሪነት ለማረጋገጥ በቅርቡ የሚገኙትን ማንኛውም የሕግ አማራጮች ሊጠቀም እንደሚችል እና ለማረጋገጥ እና/ወይም ለምርመራ ከሚገባቸው የአካባቢው ባለስልጣናት ጋር ሊያጋራ እንደሚችል ተረድቼአለሁኝ።
- **የእኔ ወይም የተማሪውን የመኖሪያ አድራሻ ለውጥ እንደዚህ ዓይነት ለውጥ ከተደረገ በኋላ በሦስት (3) የትምህርት ቀናት ውስጥ እንደማሳውቅ እስማማለሁኝ።**

ተማሪውን የሚመዘግበውን ግለሰብ ፊርማ ______________________________________________ ቀን፦ ____________________ ____________________

## ቅደም ተከተል አራት፦ ይሄንን የተሞላ ቅጽ እና የሚቀርቡ ሰነዶችን ለትምህርት ቤትዎ ይዘው ይምጡ።

***ለትምህርት ቤቱ ለቢሮ አገልግሎት ብቻ የሚውል*** ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪነት ማረጋገጫ የሚከተለው መንገድ አገልግሎት ላይ ውሏል እና/ወይም ቀርቧል። አንድ ይምረጡ።

እኔ፣ በሐሰት ወንጀል ቅጣት ስር፣ የቀረቡትን ሁሉንም ሰነዶች በግሌ እንደገመገምኩኝ እና እኔ እስከማውቀው፣ መረጃ፣ እና እምነት ድረስ ከላይ የቀረበው መረጃ እውነት ስለመሆኑ አረጋግጣለሁኝ። እንደዚሁም ከዚህ ቅጽ ጋር የሚያያዙት ሁሉም ሰነዶች በትምህርት ቤት እንደሚያዙ እና የ OSSE፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና በሚጠየቅበት ሰዓት፣ የዲሲ ጠቅላይ መምሪያ ቢሮ እና ለዲሲ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ ጨምሮ ለሌሎች ኤጀንሲዎች ተላልፈው እንደሚሰጡ አረጋግጣለሁኝ።

የትምህርት ቤቱ ሃላፊ ስም (ያትሙ) ፊርማ፦________________________________ ቀን፦ _____________ _____________

- ☐ **መንገድ ሀ፦ የትምህርት ቤቱ ሃላፊ አረጋግጧል**
  - ☐ የዲሲ የገንዘብ ድጋፍ ማረጋገጫ
  - ☐ ሆምለስ ሊያዞን የቤት አልባነት ማረጋገጫ አቅርቧል
  - ☐ የዲሲ ዋርድ
- **መንገድ ለ** የታክስ ግብር ቢሮ
- ☐ **መንገድ ሐ አንድ ሰነድ**
  - ☐ የደሞዝ ክፍያ ደረሰኝ
  - ☐ ዲሲ መንግስት የገንዘብ ድጋፍ
  - ☐ የኤምባሲ ደብዳቤ
  - ☐ ዲሲ የታክስ ቅጽ (DC Tax Form-D40)
  - ☐ የሚሊታሪ መኖሪያ ቤት ትዕዛዝ
- ☐ **መንገድ ሐ ሁለት ሰነዶች**
  - ☐ ዲሲ ሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ
  - ☐ የዲሲ መንጃ ፈቃድ ወይም መንጃ ፈቃድ ያልሆነ መታወቂያ
  - ☐ ክፍያ የተከፈለበት የክራይ ሊዝ
  - ☐ ክፍያ የተከፈለበት የፍጆታ ዕቃዎች ደረሰኝ
- ☐ **መንገድ መ** የቤት ውስጥ ጉብኝት

## የዲሲ ነዋሪነትዎን ለማረጋገጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከመንገዶቹ (ሀ-መ) አንዱን ይከተሉ።

### መንገድ ሀ

**ከትምህርት ቤቱ ሃላፊ ጋር ያረጋግጡ።**

የጎዳና ተዳዳሪ ከሆኑ፣ የዲስትሪክቱ ዋርድ፣ እና/ወይም እንደ ሜድኬድ፣ የተመጣጠኑ ምግቦች አቅርቦት እገዛ መርሀግብር ወይም ለተቸገሩ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጋፍ የመሳሰሉ የዲስትሪክቱ የሕዝብ ጥቅማጥቅሞችን መርሀግብር ላይ የሚሳተፉ ከሆነ – ትምህርት ቤትዎ መረጃዎት አለው። ከትምህርት ቤቱ ሃላፊ ወይም ከትምህርት ቤቱ ሆምለስ ሊያዘን ቢሮ ጋር ይመልከቱ።

### መንገድ ለ

**በታክስ እና ግብር ቢሮ ድረገጽ በኩል ያረጋግጡ**

በድጋሚ-የሚያስመዘግቡ ቤተሰቦች/ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የ OTR ነዋሪነትን የማረጋገጫ ሂደት በመጠቀም ለማረጋገጥ ችለዋል። ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ወይም አዋቂው ተማሪ ባለፈው የሥራ ዘመን ላይ የዲሲ ታክስ የከፈለ መሆን እና የተማሪው ማህበራዊ ደህንነት ቁጥር ያለው መሆን አለበት። በሚከተለው ድረገጽ ውስጥ ይግቡ ossedctax.com። ከዛም መረጃዎ በቀጥታ ለትምህርት ቤቱ ይላካል።

### መንገድ ሐ

**ማረጋጋጫ ሰነዶች በማስረከብ ያረጋግጡ።**

የወረቀት ቅጂዎች ያቅርቡ። ልክ እንደ የተሞላው ቅጽ የእያንዳንዱ ማስረጃዎች አድራሻ እና ስም ተመሳሳይ መሆን አለባችሁ።

**አንድ ማስረጃ ከዝርዝሩ ውስጥ ለነዋሪነት ማረጋጋጫ ያስፈልጋል።**

- ሕጋዊ የክፍያ መቀበያ ደረሰኝ የነዋሪነትን ማስረጃ ካቀረቡበት አራባ አምስት (45) ቀናት ውስጥ የቀረበ። ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ስም ወይም የአሁኑን የዲሲ አድራሻውን/ሻዋን የሚያሳይ የአዋቂ ተማሪ ስም ማካተት አለበት እና የአሁኑ የዲሲ የግል ግብር ዓመት ብቻ መያዝ እና ሌሎች ግዛቶች ያልተዘረዘሩበት።
- **ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግስት ቢሮ የተሰጠ ጊዜው ያላለፈበት የገንዘብ ድጋፍ፣** ተማሪውን ላስመዘገበው ግለሰብ ወይም ለአዋቂው ተማሪ የተሰጠ እና ለትምህርት ቤቱ በሚቀርብበት ሰዓት የአሁን የሆነ፣ ጊዜያዊ ድጋፍ ለችግረኛ ቤተሰቦች [Temporary Assistance for Needy Families (TANF)]፣ ሜድኬድ (Medicaid)፣ የግዛቱ የልጆች የጤና መድህን [State Child Health Insurance Program (SCHIP)]፣ ተጨማሪ የደህነት ገቢ (Supplemental Security Income)፣ የቤት ድጋፍ እና ሌሎች መርሀግብሮችን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰንም።
- **የተረጋገጠ የቅጽ D40** ቅጂ ከዲሲ ታክስ እና ግብር ቢሮ የተሰጠ፣ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ወይም አዋቂ ተማሪ ስም ያለበት  በጣም የቅርብ ወይም የአሁን የሆነ የግብር ዓመት የዲሲ ታክሶች የተከፈለበት ማስረጃ።
- **የአሁኑ የሚሊታሪ መኖሪያ ቤት ትዕዛዞች ወይም የሚሊታሪ የደብዳቤ ራስጌ ያለው መግለጫ፣** ሁለቱም ተማሪውን የሚያስመዘግበውን ግለሰብ ወይም የአዋቂው ተማሪ ስም፣ እና የመኖሪያ ዲስትሪክት አድራሻ ማከተት አለበት።

**ወይም**

**ሁለት ማስረጃ ከዝርዝሩ ውስጥ ለነዋሪነት ማረጋጋጫ ያስፈልጋሉ።**

- ሕጋዊ እና ጊዜው ያላለፈበት የዲሲ ሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ወይም የአዋቂው ተማሪ ስም እና የእሱ/የእሷ የአሁኑ ዲስትሪክት ቤት አድራሻ የሚያሳይ።
- ሕጋዊ እና ጊዜው ያላለፈበት የሊዝ ወይም **የቤት ኪራይ ስምምነት ለብቻው የተያያዘ የክፍያ ማስረጃ ጋር፣** ተማሪውን በሚያስመዘግበው ግልሰብ ወይም አዋቂው ተማሪ ስም የሚያሳይ ሆኖ፣ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ በትክክል የሚኖርበት ለአሁኑ የዲሲ አድራሻ፣ ቅጹ ከገባ ወዲያውኑ ለሁለት (2) ወራት ውስጥ አስቀድሞ የተዘጋጀ።
- ሕጋዊ እና ጊዜው ያላለፈበት የዲሲ ሞተር ተሽከርካሪ የከዋኞች ፈቃድ ወይም በመንግስት የተሰጠ መንጃ-ፈቃድ ያልሆነ መታወቂያ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግለሰብ ወይም የአዋቂው ተማሪ ስም እና የእሱ/የእሷ የአሁኑ ዲስትሪክት ቤት አድራሻ የሚያሳይ።
- **የፍጆታዎች ደረሰኝ** (Utility bill) **(ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ፣ እና የውሃ የክፍያ ደረሰኞች ብቻ ተቀባይነት አላቸው)እንደተከፈለ የሚያሳይ ሌላ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ ጋር፣** ይሄ ቅጽ ከገባበት ወዲያውኑ ሁለት (2) ወራት ውስጥ አስቀድሞ የተዘጋጀ፣ ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግልሰብ ስም ወይም የአዋቂውን ተማሪ ስም እና የእሱን/የእሷን የአሁኑን አድራሻ የሚያሳይ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • **የኤምባሲ ደብዳቤ** ባለፉት አስራ ሁለት ወራት (12) ውስጥ የተፃፈ። ተማሪውን የሚያስመዘግበው ግልሰብ ወይም የአዋቂውን ተማሪ ስም እና የኤምባሲው የቢሮ ማህተም ማካተት አለበት። እንክብካቤ ሰጪው እና ጥገኛው ተማሪ ወይም አዋቂው ተማሪ በዲሲ ውስጥ የኤምባሲው ንብረት ውስጥ ወይም በሚመለከተው የትምህርት ዓመት የዲሲ ንብረት ውስጥ የሚኖር መሆን አለበት። | | |
| መንገድ **መ** | **በሌላ አማራጭ መንገድ በኩል ያረጋግጡ።** ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች በአንዳቸውም ቢሆን ማረጋገጥ ካልቻሉ፣ ስለ የቤት ጉብኝት የትምህርት ቤቱን ሃላፊ ያነጋግሩ። | | |

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የትምህርት ዓመት 2019/2020 ስምምነቶች

ለዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ስለሚከተሉት ምርጫዎችዎን ለማሳወቅ **በዚህ ቅጽ ይጠቀሙ።** 1) የተማሪዎን መረጃዎች ለብዙኃን መገናኛዎች ለማካፈል፣ 2) ለተማሪዎ ማኅበራዊ ስሜታዊ ግልጋሎቶች ለማበርከት፣ እና 3) የተማሪ ልጅዎን መረጃዎች ለውትድርና መልማዮች እንዲሰጡ ለማድረግ።

| የዲሲፒኤስ ተማሪ | |
|---|---|
| **የመጀመሪያ ስም፤** | **የመጨረሻ ስም፤** |

## እንደ ምርጫ – ለብዙኃን መገናኛዎች መፍቀድ እና እንዲሰጥ መስማማት

ከዚህ በታች በመፈረም፣ ከዚህ ቀጥየ ዲሲፒኤስ እና ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ ሠራተኞቻቸውን እና ወኪሎቻቸውን፣ ተተኪዎቻቸውን፡ እና ተመዳቢዎቻ ቸውን ጨምሮ፡ (1) የተማሪየን ምስል እና ድምፅ እንዲቅርጹ፣ (2) በራሳቸው ፍላጎትና ውሳኔ መሠረት እነዚህን የተቀረጹ ምስል እና ድምፅ ቅኝት (edit) እንዲያደርጉ፣ እና (3) እነዚህን የተማሪየን የተቀረጹ ምስሎች እና ድምፆች ከጥበብ እና ከጽሁፍ ሥራዎች ጋር በቪዲዮ ቴፕ፣ በፎተግራፎች፣ በዲጂታል ሚዲያ፣ እና በማንኛውም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ወይንም የኅትመት ሚዲያ ጭምር እንዲቀረጹ ከዚህ ቀጥየ ፈቃድ ሰጥቻለሁ። ይህ ፈቃድ መስጠት ዲሲፒኤስን ወይንም ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያን ጨምሮ ማናቸውንም የልጄን የሕይወት ታሪክ ወይንም ሌሎች መለያ የሆኑ መረጃዎችን በሚመለከት ይፋ ለማውጣት ፈቃድ የማልሰጥ ሲሆን ትምህርት ቤቴን በማነጋገር ስምምነቱን በማናቸውም ጊዜ ማገድ ወይንም ማንሣት እንደምችል እረዳለሁ።

ከዚህ ቀጥየ ዲሲፒኤስ እና ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ ሠራተኞቻቸውን እና ወኪሎቻቸውን፣ ተተኪዎቻቸውን፡ እና ተመዳቢዎቻቸውን እና በልጄ ምስል እና /ወይንም ድምፅ፣ የጥበብ ሥራ፣ እና/ወይንም በጽሁፍ ሥራ የሚጠቀም ማናቸውም አካል፣ በዚህ የፈቃድ ስምምነት መሠረት፣ እኔ ወይንም ልጄ ካለብን ወይንም ሊኖርብን ከሚችል ከማንኛውም ወይንም ከሁሉም የይገባኛል ተጠጥያቂነት፣ ጥፋት፣ ዋጋዎች እና ወጭዎች ነጻ ስለመሆን ወይንም ከዚህ በኋላ ለፈጠሩ ስለሚችሉ ጉዳዮች ሊኖረኝ ስለሚችል ወይንም ልጄ ሊኖረው ሰለሚችሉ ጉዳዮች ተጠያቂነት ነጻ አድርጌአቸዋለሁ።

የመረጃዎች የመለቀቅ ሁኔታ በህግ የተከበረ መሆኑ ይገባኛል። ይህ ስምምነት እስከ ዓመቱ ትምህርት ማብቂያ ድረስ ዋጋ ያለው ሲሆን በማናቸውም ጊዜ ስምምነቱን ማንሳት ወይንም ማገድ ይቻላል።

☐ እስማማለሁ ☐ አልስማማም

የወላጅ/የአሳዳጊ ስም፤ ______________________ ፊርማ፤ ______________________ ቀን፤ ____________

## እንደ ምርጫ – ለውትድርና መልማዮች መረጃዎች ይፋ ማድረግ (ከ 6ተኛ እስከ 12ተኛ ክፍል)

ከዚህ በታች በመፈርም የተማሪ ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ (ወይንም ተማሪው ለአቅመ አዳም የደረሰ ከሆነ) መረጃዎች ይፋ እንዳይወጡ የማገድ ምርጫ ካላደረገ በስተቀር፣ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ዲሲፒኤስ ከ 6ተኛ እስከ 12ተኛ ክፍል የተማሪዎችን፣ ስም፣ አድራሻ፣ እና የስልክ ቁጥር ("መረጃ") ለውትድርና አገልግ ሎት መልማዮች እንዲሰጥ ፌድራላዊ ህጎች ይጠይቃሉ። ይህ ስምምነት ተማሪ ልጅዎ በዲሲፒኤስ ተመዝግቦ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ጸንቶ የሚቆይ ሲሆን፣ በማንኛውም ጊዘ ስምምነቱን ማገድ ወይንም ማንሣት ይቻላል።

☐ ዲሲፒኤስ የተማሪየን/የእኔን (ተማሪው ለአቅመ አዳም የደረሰ ዐዋቂ ከሆነ) መረጃዎች ለውትድርና መልመዮች እንዳይሰጥ እጠይቃለሁ።

የወላጅ/የአሳዳጊ ስም፤ ______________________ ፊርማ፤ ______________________ ቀን፤ ____________

## እንደ ምርጫ – ማኅበራዊ ስሜታዊ የጤና አግልግሎቶች

ዲሲፒኤስ፣ ጫናን፣ ኀዘንን፣ ቁጣን፣ ወይንም ተማሪዎች ህይወት ላይ ጫና የሚያሳድሩ ሌሎች ስሜቶች የሚሰማቸውን ተማሪዎች ለመረዳት ዲሲፒኤስ በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠኑ ሙያተኞች አሉት። የተማሪዎን የግል መብት ለመጠበቅ፣ ዲሲፒኤስ ለሁሉም የግላዊነት መብቶች መመሪያዎችን ጠብቆ በማክበር ይይዛል። ከዚህ በታች በፈረም፣ የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤት ባለሙያዎች ከተማሪዎ ጋር የመሥራቱን ሂደት እንዲጀምሩ ሥልጣን ይሰጣሉ። ለአገልግሎቶቹ እጅግ በጣም ጥሩው ከአሠራር ልምዶች ጋር ከሚጣጣሙ ከማንኛውም እቅድ ጋር እንዲተዋወቁ እና እንዲታከሉም ይደረጋል። የተማሪዎ መረጃ፣ በትምህርት ቤት የአእምሮ ጤንነት ቡድን እንዲጣራ በማድረግ በምሥጢር ተጠብቆ እንዲያዝ ይደረጋል። ይህ ስምምነት እስከ ትምህርት ዓመቱ ማብቂያ ድረስ ጸንቶ የሚቆይ ሲሆን በማናንኛውም ጊዜ ስምምነቱን ማገድ ወይንም ማንሣት ይቻላል።

የሚስማሙ ከሆነ፣ ከሚከተሉት ውስጥ ልጅዎ ያለበት ችግር የትኛው እንደሆነ እባክዎን ምልክት ያድርጉ።

☐ የወላጆች ፍቺ/መለያየት ☐ ቤት የለሽነት ☐ በማደጎ ሥር መኖር

☐ በእስር ላይ ያለ ወላጅ ☐ የቅርብ ቤተሰብ ሞት ☐ ሌሎች ችግሮች፤ ______________________

ስለእነዚህ ጉዳዮች ከት/ቤት የአእምሮ ጤንነት ቡድን ጋር በስፋት ለመወያየት ከአባላቱ ኣንዱ እንዲያነጋግሩዎት ይፈልጋሉ? ☐ አዎን ☐ የለም

**የወላጅ/የአሳዳጊ ስም፤** ______________________ **ፊርማ፤** ______________________ **ቀን፤** ____________

MY SCHOOL DC

The Public School Lottery

MySchoolDC.org

# የወንበር መቀበያ ቅጽ
# 2019-20 የትምህርት ዓመት

**ወላጅ/አሳዳጊ፡-** የ My School DC ሎተሪ ላይ የተሳተፉ ከሆነ፣ እባክዎ የልጅዎን My School DC ትምህርት ቤት ውስጥ ያገኙትን ወንበር የተቀበሉ ከሆነ ይሄንን ቅጽ ይሙሉት እና  ከሌሎች የመመዝገቢያ መስፈርቶች ጋር ትምህርት ቤቱ ጋር በአካል በመምጣት ያስረክቡት።

## የተማሪ መረጃ

በ My School DC ሎተሪ ላይ ለተሳተፉት እያንዳንዱ ልጆች አንድ ቅጽ መሙላት አለብዎ።

| | |
|---|---|
| **የመጀመሪያ ስም እና የአያት ስም፡-** | **የትውልድ ቀን (ወር/ቀን/ዓመት)፡-** |
| **የአሁኑ ትምህርት ቤት (2018-19)፡-** | **የአሁኑ ክፍል (2018-19)፡-** |
| **የተመዘገበበት ትምህርት ቤት (2019-20)፡-** | **የተመዘገበበት ክፍል (2019-20)፡-** |

## መዝገቦች ተለቋል

እባክዎ የሚመዘገቡበት ትምህርት ቤት የልጅዎን መዝገቦች መጠየቅ እንዲችል እዚህ ቅጽ ስር ላይ የተፃፈውን አንብበው ይፈርሙበት።

ይሄ ቅጽ ላይ በመፈርም፣ ከዚህ በላይ ላለው ተማሪ አሁን ካለበት ትምህርት ቤት የሚገባበት ትምህርት ቤት መዝገብ እንዲጠይቅ  ከዚህ ጀምሮ ሥልጣን ሰጥቸዋለሁ። ከዚህ በላይ የተገለጸውን ተማሪ በተመለከተ ከዚህ በፊት ከተማረባቸው ከማንኛውም ከሌሎች ትምህርት ቤቶች መዝገቦቹን እንዲጠይቅ የሚገበበት ትምህርት ቤት እንዲጠይቅ ፈቃድ ሰጥቸዋለሁ። የሚገባበት ትምህርት ቤት በተጨማሪ ለሌላ ሦስተኛ አካል ወይም ኤጄንሲ ከእኔ በጽሑፍ ከተገለጸው  ስምምነት ውጪ በቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና የግል መብት አዋጅ ሥልጣን በስተቀር (FERPA) (20 U.S.C. § 1232g; 34 CFR Part 99) እንደማያስተላለፈ ወይም እንደማይሰጥ አውቀያለሁ።

## የምዝገባ ማረጋገጫ

እያንዳንዱን ዓረፍተ ሐሳብ እንደተረዱት እና ለ 2019-20 ዓ.ም የልጅዎን ምዝገባ ለማረጋገጥ የዚህ ቅጽ ስር ላይ የተፃፈውን ያንብቡ እና ይፈርሙ።

ለ 2019-20 ዓ.ም ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ መመዝገብ እንደማልችል ተረድቼአለሁኝ እና ከላይ የተጠቀሰው “የሚመዘግበው ትምህርት ቤት” ላይ መመዝገቤን አረጋግጣለሁኝ።

ይህ ቅጽ አንዴ ካስረከብኩ፣ በአሁኑ ትምህርት ቤት ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት (2019-20) ቦታዬን እንደሚሰጥ እና የአሁኑ ትምህርት ቤቴ ቦታዬ ለሌላ ቤተሰብ እንደሰጥ እንደሚነገረው እረዳለሁ።

ከዚህ ትምህርት ቤት መጠባበቂያ ላይ ዕድል አግኝቼ የተመዘገብኩኝ ከሆነ ከ My School DC ማመልከቻ ላይ ከዚህ ትምህርት ቤት ታች ላይ ከተዘረዘሩት ሁሉም ትምህርት ቤቶች መጠባበቂያ ላይ እንደምሰረዝ አውቄአለሁኝ።

## ወላጅ/አሳዳጊ መረጃ

ይሄ ቅጹን የሚሞላው ተመሳሳይ ሰው መሆን አለበት።

**ፊርማ፡-:**______________________________ **የታተመ ስም፡-:**________________________ **ቀን:** __________________

**FOR OFFICE USE ONLY** **Application Tracking #:** _______________________________________

# የትምህርት ዓመት 2019/2020 ማሳሰቢያ

**ይህ መረጃ** የወላጆችን/የአስዳጊዎችን እና የዲሲፒኤስ ተማሪዎቻቸውን መብቶች ይዘረዝራል።

## የ 2015 እያንዳንዱ ተማሪ ትምህርቱ የሚሳካለት ይሆናል ህገ ደንብ

ይህ ማሳሰቢያ እያንዳንዱ ተማሪ ትምህርቱ የተሳካለት ይሆናል በተሰኘው የ 2015 ህገ ደንብ (Every Student Succeeds Act of 2015) መሠረት፣ የልጅዎን የክፍል መምህራን የሙያ የብቃት ደረጃ የመጠየቅ መብት እንዳለዎት የሚገጽልዎት ነው። በማናቸውም ጊዜ የሚከቱሉትን መረጃዎች የመጠየቅ መብት አለዎት።

- አንድ መምህር ለሚያስተምርባቸው የክፍል ደረጃዎች እና ሊሚያስተምራቸውም የትምህርት ዐይነት መስኮች የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያን የመምህር እና የሊቸንሳ ፈቃድ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሆኖ መገኘት አለመገኘቱ፤
- አንድ መምህር በአስቸኳይ ጊዜ ወይንም በሌሎች ጊዜያዊ ሁኔታ ያስተምር እንደሆነና ወይንም የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የትምህርት ደረጃ እና የሊቼንሳ መስፈርት ሁኔታ እንዲነሱ ተደርገው እንደሆነ፤
- አንድ መምህር የሙያ የምስክር ወረቀት ባገኘበት የትምህርት መስክ ያስተምር እንደሆነ፤
- .አንድ ተማሪ አገልግሎቶች የሚሰጠው በሙያው በሚገባ ባልሠለጠኑ (paraprofessionals) (ሥልጠና ባላገኙ በመምህር ምልከታ ክትትል ሥር ያሉ የመምህሩ የረዳቶች) መሆን አለመሆናቸው እና፣ ከሆነም የሙያ ሥልጠና የሌላቸው ረዳቶች የሙያ ደረጃቸው።

እባክዎን የተጠየቁትን ሁሉ እና ከዚህ ማስታወሻ ጋር ያዘመዱዋቸውን ማናቸውንም ሌሎች ጥያቄዎች ሁሉ ለዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በ dcps.hrdataandcompli -ance@dc.gov ኢሜይል ያድርጉ ወይንም በ (202) 535-2483 ፋክስ ይላኩ።

## የተማሪ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ

ይህ ማስታወሻ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎችን (ለአቅም አዳም ደርሰዋል ተብለው የተገመቱ ልጆች ወይንም 18 ዓመት እና ከዚህም በላይ በሆነ እድሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች) አሰሳ መጠየቆችን ስለማካሄድ እና ስለ ሰውነት ምርመራዎች/ስለ ማጣሪያዎች እና በግላዊ መረጃዎች ለገበያ ንግድ አገልግሎቶች የመጠቀም መብቶች ይገልጻል። እነዚህ መብቶች፣ በተማሪ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ (20 U.S.C. § 1232h; 34 CFR Part 98) ("PPRA") ላይ የተብራሩ ሲሆን፣ በመረጃው ውስጥም እንዲቀርቡ ተደርገዋል። በአሰሳ መጠይቆች ሥራ ላይ መዋል እና መረጃዎች አሰባሰብ፣ የመረጃዎቹን ውጤት ይፋ የማድረግ እና በግላዊ መረጃዎች ለንግድ፣ ለሽያጭ ወይንም ለሌላ የስርጭት አገልግሎቶችን በሚመለከት ዲሲፒኤስ ፖሊሲዎችን ነድፏል፣ ሥራ ላይም እንዲውሉ አድርጓል። በ https:// dcps.dc.gov/surveys ላይ የሚገኘው የዲሲፒኤስ የአሰሳ መጠይቅ የክንውን ቀናት፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መሠረት፣ በምሥጢር ስለሚጠበቁ የአሰሳ መጠይቅ መረጃዎች እና በተማሪዎች ላይ ስለሚካሄዱ የሰውነት ምርመራዎች/ማጣሪያዎች ውጤት ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው ለሚገኙ ተማሪዎች ያሳውቃል። ለሰውነት ምርመራዎች/ማጣሪያዎች ሁሉ ልጆቻቸው እንዳይሳተፉ እና ከክንዋኔዎቹ ሁሉ እንዲላቀቁ በመግለጽ ፈርመው ውሳኔዎቻቸውን በጽሑፍ (passive consent) እንዲያቀርቡ የሚያስፈልጋቸው ወላጆች፣ አሳዳጊዎች ወይንም ብቁ ሆነው ለሚገኙ ተማሪዎች፣ ምርጫዎቻቸውን እንዲያመለክቱ ዲሲፒኤስ ቅጾችን ያቀርባል። እንደ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ወይንም ብቁ እንደሆነ ተማሪ፣ በ PPRA ሥር የሚከተሉት መብቶች ይኖሮዎታል።

1. **ለአሰሳ መጠይቅ ስምምነት።** ተማሪዎች በሙሉም ይሁን በከፊል በ ዩኤስ የትምህርት መምሪያ (USDE) የገንዘብ ድጋፍ በሚካሄድ አሰሳ መጠይቅ ፕሮግራም ወላጆች /አሳዳጊዎች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ከማስፈለጉ በፊት ስምምነታቸውን መግለጽ ያለባቸው እና በምሥጢር የተያዙ መረጃዎች እና አሳሳቢ ሁኔታዎች ከሚከተሉት ውስጥ ሁሉንም ወይንም እንዱን የሚመለከት ነው፤
    - የተማሪው ወይንም የተማሪው ወላጅ የፖለቲካ ወገናዊነት ወይንም እምነት፤
    - የተማሪው ቤተሰቦች አእምሯዊ ወይንም ሥነ ልቦናዊ ችግሮች፤
    - ስለ ጾታዊነት የሚሰጥ እሴት ወይንም ስለ ግብረ ሥጋ ንክኪነት አመለካከት፤
    - ህጋዊነት የሚጎለው፣ ፀረ ማኅበራዊ፣ ራስን የሚያስወነጅል ምስክርነት መስጠት (self-incriminating), ወይንም ራስን የሚያዋርድ ባህርይ ማሳየት"፤
    - ቤተ ሰብአዊ የቅርብ ግንኙነቶች ያሏቸው መልስ ሰጭዎች ስለ ሌሎች ያሏቸው ወሳኝ ግምቶች፤
    - እንደ ጠበቆች፣ ዶክተሮች፣ ወይንም የቤተ ክህነት ሰዎች የመሳሰሉ ህግ የሚያውቀው እና የተቀበለው ተዛምዷዊ በምሥጢር የሚጠበቁ ግንኙነቶች፤
    - ሀይማኖታዊ ክንዋኔዎች፣ መደባዊ ግንኙነቶች፣ ወይንም የተማሪው ወይንም የወላጆች እምነቶች፣ እና
    - የፕሮግራም ብቁነትን ለመወሰን በህግ ከሚያስፈልገው ሌላ።
2. **የማገድ ችሎታ።** ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች ከሚከተሉት ተማሪን ዘወትር የማገድ ወይንም የማግለል እድሎች አሏቸው፤
    - በ ዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት መምሪያ(USDE) የገንዘብ ድጋፍ ያልተደጎመ ማንኛውም የአሰሳ መረጃ
    - አስቸኳይ ያልሆነ፣ ማንኛውም የሰውነት ማጋለጥን ወይንም መብጣት መቅደድን የመሳሰሉትን የሚጠይቅ የሰውነት ምርመራ (invasive physical exam) ወይንም ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር በትምህርት ቤት ሥራ ላይ የሚውል ወይንም በወኪሉ አማካይነት የሚከናወን ወይንም ከትምህርት ቤት የመገኘት ሁኔታ የተማሪን የቅርብ የጤንነት እና የሠላም ደህነት ሁኔታ ለመጠበቅ ሳይሆን (የመስማት፣ የማየት፣ እና የጀርባ አጥንት መጉበጥ (scoliosis) ማጣሪያዎች እና ማንኛውም የስቴት ህግ ከሚጠይቀው የአካል ምርመራ/ማጣሪያ በስተቀር)፣ እና
    - ማሰባሰብን፣ ይፋ ማድረግን፣ ወይንም ማናቸውም ክንዎኖች፣ ወይንም ከተማሪዎች ለንግድ ሥራ ገበያ ሽያጭ፣ ወይንም ለስርጭት አገልግሎት ተግባር ብቻ የተሰበሰቡ ግላዊ መረጃዎችን፣ ወይንም ለስርጭት አገልግሎት የሚያካትቱ (ይህ ለማሰባሰብ፥ ለማሰራጨት፣ ወይንም ከተማሪዎች የተሰበሰቡ ግላዊ መረጃዎችን፣ ለመንደፍ፣ ለመመዘን፣ ወይንም ለተማሪዎች ወይንም ለትምህርት ተቋማት የትምህርት ምርት ውጤቶችን ወይንም አገልግሎቶችን ማቅረብን ለተሰበሰቡ ግላዊ መረጃዎች አገልግሎት ተግባር አያገለግልም።)
3. **የመመርመር መብት።** ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ጥያቄ ሲቀርብ እና ሥራ ላይ ከመዋላቸው ወይንም አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት፣ ማጣራት ይችላሉ፤
    - በምሥጢር ተጠብቀው የተያዙ የተማሪዎች እና በሦስተኛ አካላት የተዘጋጁ አሰሳ መጠይቆች መረጃዎች፤,
    - ለማንኛውም ለገበያ ሽያጭ፣ ወይንም ለሌሎች የማከፋፈያ አገልግሎቶች ግላዊ መረጃዎችን ለማሰባሰብ አገልግሎቶች የሚውሉ መጠይቆች፤ እና
    - እንደ ሥርዓተ ትምህርት አካል መገልገያ የሆኑ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች።

መብቶቻቸው ተጥሷል ብለው የሚያምኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በሚከተሉት አድራሻዎች የአቤቱታዎች ክስ ማቅረብ ይችላሉ፤ Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Avenue, S.W., Washington, D.C. 20202.

## የወላጅ የትምህርት መብቶች እና የግል መረጃዎች የመጠበቅ መብት ድንጋጌ

የወላጅ የትምህርት መብቶች እና የግል መብት ድንጋጌ (The Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና እድሜአቸው 18 እና ከዚህ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ("ብቁ የሆኑ ተማሪዎች") የተማሪን የትምህርት መረጃዎች በሚመለከት የተወሰኑ መብቶች አሏቸው። ይህ የጽሁፍ ሰንድ በግልጽና በዝርዝር የተቀመጡ፡ ያለዎትን በጣም አስፈላጊ መብቶች ለማሳወቅ የቀረበ ነው።

1. **የተማሪውን የትምህርት መረጃዎች የመርመር እና የማጣራት መብት** መረጃዎቹን ለማግኘት ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) በ 45 ቀናት ውስጥ ጥያቄ ይደርሰዋል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይንም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ለመርመር የሚፈልጉትን (ዓቸውን) መረጃዎች የሚገልጽ የጽሑፍ ጥያቄ ለትምህርት ቤቱ ርእሠ መምህር ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የትምህርት ቤቱ ርእሠ መምህር ወይንም ሌላ ተገቢ የሆነ የትምህርት ቤት ባለሥልጣን መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል ሁኔታዎችን በማመቻቸት ወላጅን/አሳዳጊን ወይንም ብቁ የሆነን ተማሪ መረጃዎቹ ስለሚመረመሩበት ጊዜ እና ቦታ ያስታውቃል።

2. **የተማሪውን የትምህርት ማስረጃዎች እንዲስተካከሉ የመጠየቅ መብት** ወላጅ/አሳዳጊ ወይንም ብቁ ሆኖ የሚገኝ ተማሪ በ FERPA ሥር የትምህርት ማስረጃዎቹ ትክክል አይደሉም ወይንም ያሳስታሉ ወይንም የተማሪውን የግል መብት ያዛባሉ ብሎ የሚያምንን የሚመለከት ነው። ወላጅ/አሳዳጊ ወይንም ብቁ ሆነው የሚገኝ ተማሪ ለትምህርት ቤት ርእሠ መምህር፣ እንዲለወጥ ስለሚፈልጉት የትምህርት መረጃው ክፍል በትክክል በመለየት እና በማብራራት ለምንስ መለውጥ እንዳስፈለገ በግልጽ ሊጽፉ ይገባል። በወላጅ/አሳዳጊ ወይንም ብቁ በሆነው ተማሪ እንደ ተጠየቀው፣ ዲሲፒኤስ መረጃውን ላለማስተካከል ከወሰነ፣ ትምህርት ቤቱ ለወላጅ/አሳዳጊ ወይንም ብቁ ለሆነው ተማሪ፣ ስለ ውሳኔው በመንገር ለማስተካከል ስለተጠየቀው ጉዳይ በችሎት እንዲታይላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ይመከራቸዋል። በፍርድ የመታየቱን የአቀራረብ ቅደም ተከተል ተጨማሪ መረጃ ለወላጅ/አሳዳጊ ወይንም ብቁ ሆኖ ለሚገኝ ተማሪ በፍርድ እንዲታይ ለማድረግ ያላቸው መብታቸው በሚገለጽላቸው ጊዜ እንዲያውቁ ይደረጋል።

3. **የግል መለያ የሆኑ መረጃዎች ይፋ እንዲወጡ (በጽሁፍ) የመስማማት መብት** ሲሆኑ እነዚህም የ FERPA ባለሥልጣናት ያለስምምነት ይፋ ሊያወጧቸው ከሚችሏቸው በስተቀር በተማሪው የትምህርት መረጃዎች ውስጥ የሚገኙትን ነው። ለምሳሌ፣ ተማሪው ለመመዝገብ በሚፈልግበት ወይንም በተመዘገበበት ትምህርት ቤት እና የተማሪውን የትምህርት መረጃዎች ይፋ ማድረግ ለተማሪው ምዝገባም ሆነ ለዝውውር ተግባር አገልግሎት በሚጠየቅበት ጊዜ ዲሲፒኤስ ያለስምምነት ለሌላ ትምህርት ቤት ወይንም ለሌላ ትምህርት ቤት ወረዳ ባለ ሥልጣናት መርጃዎቹን ይፋ ያደርጋል። በተጨማሪም፣ ዲሲፒኤስ ህጋዊ ትምህርት ነክ ዝንባሌዎች ይኖራቸዋል ብሎ ለሚያስባቸው ባለሥልጣናት FERPA የትምህርት መረጃዎች ያስምምነት ፈቃድ ይፋ እንዲወጡ ሊያዝ ይችላል። የትምህርት ቤት ባለሥልጣን በዲሲፒኤስ አስተዳዳሪ፣ ሱፐርቫይዘር፣ አስተማሪ፣ ወይንም ረዳት አባል ሆኖ የተቀጠረ ሠራተኛ (የጤና ወይንም የህክምና ባለሙያ እና የህግ አስከባሪ አባል ሠራተኞችን ጭምሮ)፣ ዲሲፒኤስ፣ ልዩ ሥራ እንዲያከናውን የተኮናተረው (እነደ የህግ ጠበቃ፣ ኦዲተር፣ የህክምና ባለሙያ፣ ወይንም ፈውስ ሰጪ (therapist) የመሳሰሉትን)፣ እንዲያከናውን የተኮናተርው ሰው ወይንም ኩባንያ፣ ወይንም ወላጅ/አሳዳጊ፣ ተማሪ ወይንም ለምሳሌ በሥነ ሥርዓት ወይንም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ወይንም በኦፊሴላዊ ኮሚቴ፣ ወይንም ኃላፊነቱን ወይንም ኃላፊነቷ ለመወጣት ለሚያገለግል ወይንም ለምታገለግል ለሌላ ትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ሥራ የሚያግዝ ተማሪ ወይንም ሌላ የበጎፈቃድ ሠራተኛ ነው። የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ሙያዊ ኃላፊነቱን ወይንም ኃላፊነቷን ለመወጣት የትምህርት ማስረጃዎችን ለመመርመር ከፈለገ ወይንም ከፈለገች ህጋዊ ትምህርታዊ ፍላጎቶች አሉት ወይንም አሏት ማለት ነው።

4. **አቤቱታ የማቅረብ መብት** ዩኤስ የትምህርት መምሪያ ከ FERPA ጋር መሟላት የሚገባቸውን ጉዳዮች በሚመለከት ዲሲፒኢስ አላሟላም ተብሎ የተከሰሰበትን ጉዳይ በሚመለከት። FERPA ን የሚያስተዳድር ጽሕፈት ቤት ስም እና አድራሻ እንደሚከተለው ነው፤ Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Ave. SW, Washington, DC 20202.

5. **ተማሪውን የማይጎዱ መረጃዎች (directory information) ይፋ እንዳይወጡ የመጠበቅ መብት።** በራሱ መብት መሠረት፣ ዲሲፒኤስ "የማይጎዱ መረጃዎች" በአጠቃላይ ጎጂ ናቸው ተብለው የማይገመቱ ወይንም የግልን መብት የማይጻረሩ መሠረታዊ መረጃዎች በዲስትሪክቱ ህግ እና FERPA መሠረት ያለ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይንም ብቁ የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የፈቃድ ስምምነት ይፋ ማድረግ ይችላል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይንም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ከታች የተመለከተውን መረጃ ይፋ ማድረጊያ መፍቀጃ ጎጂነት የሌላቸውን የተማሪ መረጃዎች ቅጽ በመሙላት ዲሲፒኤስን ከላይ ከተገለጹት መረጃዎች መካከል ጎጂነት የሌላቸውን ጥቂቶቹን ወይንም ሁሉንም ይፋ እዳያወጣ ማሳወቅ ይችላሉ።

### እንደምርጫ – ጎጂነት የሌላቸው የተማሪው መረጃዎች ይፋ እንዲውጡ አያድርጉ።

ዲሲፒኤስ ይፋ የሚያወጣውን መረጃ ለማገድ ምርጫ ሊያደረጉ ይችላሉ። ያለ እርስዎ ስምምነት ዲሲፒኤስ ከዚህ በታች ይፋ እንዲያደርጋቸው የማይፈልጓቸው መረጃዎች ካሉ እባክዎን ምልክት ያድርጉባቸው።

- ☐ የተማሪው ስም
- ☐ የተማሪው አድራሻ
- ☐ የወላጅ/የአሳዳጊ ኢሜይል
- ☐ የክፍል ደረጃ
- ☐ በኦፊሴል በታወቁ ክንዋኔዎች እና ስፖርቶች
- ☐ የአቴሌትክ ቡድኖች አባላት ክብደት እና ቁመት
- ☐ በፊት የተማረባቸው ትምህርት ቤቶች ስም
- ☐ ተማሪው የተወለደበት ዘመን እና የትውልድ ቦታ
- ☐ የተሰጡት ዲፕሎማዎች/ሽልማቶች
- ☐ የተማረባቸው ቀናት
- ☐ የተማሪው ስልክ ቁጥር
- ☐ የሚምርበት ትምህርት ቤት ስም

ከዚህ በታች በፈረም፣ የሚከተሉትን አረጋግጣለሁ፤

- ዲሲፒኤስ ከላይ ምልክት ያደረኩባቸውን በሚመለከት ምንም ዐይነት መረጃ ይፋ አያደርግም፤
- ምልክት ያላደርኩባቸውን ማናቸውንም መረጃዎች ከዚህ ቀጥየ ዲሲፒኤስ ይፋ እንደሚያደርግ እስማማለሁ፤ እንዲሁም
- ይሁን እንጂ፣ ማድረግ የሚያስፈልግ ከሆነ ወይንም በ FERPA ሥር የሚፈቀድ ከሆነ ዲሲፒኤስ ይህንን መረጃ ይፋ ሊያደርግ እንደሚችል እረዳለሁ።

**የወላጅ/የአሳዳጊ ስም፤** ______________________________ **ፊርማ፤** ____________________ **ቀን፤** __________

# የትምህርት ዓመት 19/20 ምግብ እንዲመቻች መጠየቂያ ቅጽ

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

ለትምህርቱ ዓመቱ፣ ተማሪ ልጅዎ ስለሚያስፈልገው የአልሚ ምግብ አቅርቦት ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ለማሳሰብ **በዚህ ቅጽ ይጠቀሙ።** ይህ ቅጽ የተማሪን የጣእም ፍላጎት ምርጫዎች ለማርካት ታስቦ የቀረበ አይደለም። **እባክዎን ይህንን ቅጽ ለልጅዎ ትምህርት ቤት የጤና ሞግዚት ያስረክቡ።** ሁሉ ነገር ተሳክቶ ጥያቄዎ ሲሟላ በኢሜይል አማካይነት የምግብ አገልግሎት ባለሙያ ያነጋግርዎታል።

## ሀ. የተማሪው መርጃ

| | | |
|---|---|---|
| **የመጀመሪያ ስም፤** | **የመጨረሻ ስም፤** | **የትውልድ ዘመን፤** |
| **የትምህርት ዓመት 2019/2020 የትምህርት ቤት ስም፤** | | **የተማሪ መታወቂያ ቁጥር፤** |

**ለትምህርት ዓመቱ የክፍል ደረጃ 2019/2020:** *(አንዱ ላይ ብቻ ምልክት ያድርጉ)*

☐ Pre-K3 ☐ Pre-K4 ☐ መዋዕለ ሕጻናት ☐ 1st ☐ 2nd ☐ 3rd ☐ 4th ☐ 5th
☐ 6th ☐ 7th ☐ 8th ☐ 9th ☐ 10th ☐ 11th ☐ 12th ☐ የጎልማሶች ትምህርት

## ሀ. የተማሪው የምግብ ማመቻቸት። *በሚመለከተው ላይ ምልክት ያድርጉ።*

☐ **ሀ. የወተት ምትክ፤** ተማሪው በህክምና ምክንያት ወይንም በሌላ ልዩ አልሚ ምግብ የአቅርቦት መሟላት ፍልጎት ምክንያት የተነሣ የወተት ምትክ ለማግኘት እየጠየቀ ነው። የዩኤስዲኤ (USDA) የአልሚ ምግብ ተሟልቶ የመገኘት ፍላጎትን የሚያሟላ ሆኖ እስተገኘ ድረስ ዲሲፒኤስ የተለየ፣ የተወሰነ የወተት ምትክ ለመምረጥ የራሱ ግምት እና ውሳኔ አለው። የፍራፍሬዎች ጭማቂ እንደወተት ምትክ ተደረጎ ሊሰጥ አይችልም። የዲሲፒኤስ ምግብ ቤቶች ከነት ነጻ (nut-free items) የሆኑ ምግቦችን ብቻ ስለሚያቀርቡ፤ ከነት የሚሠሩ ወተቶች አይገኙም።

☐ **ለ. የፍልስፍና ማመቻመቻች፤** በፍልስፍና ምክንያት፣ ለምሳሌ የአትክልት ምግብ ተመጋቢ በመሆኑ ምክንያት፣ ተማሪው ምግብ እንዲመቻችለት እየጠየቀ ነው። **የምግብ መመሪያ፣ ሊተው የሚገባቸውን ምግቦች ዝርዝር ጨምሮ፤** ________________________________________

______________________________________________________________

☐ **ሐ. የምግብ አለመስማማት/ህክምና እንዲመቻች ማድረግ፤** ተማሪው በምግብ አለመስማማት ምክንያት(ቶች) የተነሣ አልሚ ምግብ እንዲመቻችለት እየጠየቀ ነው። የዲሲፒኤስ ምግብ ቤቶች በሙሉ ከነት ነጻ (nut-free items) የሆኑ ነገሮችን እንደሚያቀርቡ እባክዎን ይረዱ። ***ከዚህ በታች ያለውን ክፍል የህክምና ባለሙያ መሙላት ይኖርበታል።***

**የተማሪው የህክምና ሁኔታ ምንድን ነው፣ ምግቡንስ የሚወስነው ለምንድን ነው?** *(ምሳሌ፣ ታይፕ 1 የስኳር በሽታ፥ ስንዴ ወይንም ዓሣ ምግብ መጣላት)*

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**የምግቡ ሁኔታ** ☐ መደበኛ ☐ የተከታተፈ ☐ የተፈጨ ☐ የላመ

**የምግብ መጣላት አየር ወልድ ነው?** ☐ አዎን ☐ የለም

| መተው ያለባቸው ምግቦች፤ | ምትክ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

የሚ

በሀ
C

ለአ

**የህምናው ጽሕፈት ቤት ማኅተም**

**የህክምና ባለሙያው ስም፤** ____________________________

**የህክምና ባለሙያው ፊርማ፤** ____________________________

**ቀን፤:** ____________ **የህክምናው ባለሙያ መታወቂያ** ________________

## ሀ. የወላጅ/የተንከባካቢ ፊርማ

ከላይ የቀረበው መረጃ፣ እስከማውቀው ድረስ በሙሉ ትክክል እንደሆነ አረጋግጣለሁ። በዚህ ቅጽ ላይ የሰፈረው መረጃ ቅጹን ለተቀበሉበት የትምህርት ዓመት ማብቂያ ድረስ በሥራ ላይ እንደሚቆይ እረዳለሁ። በልጄ የህክም እና/ወይንም የሚያስፈልገው የአልሚ ምግብ አቅርቦት ፍላጎት ለውጦችን እንዲያንጸባርቅ ይህንን ቅጽ ጊዘውን ጠብቆ የሚጓዝ እንዲሆን እየተቃና እንዲገኝ አደርጋለሁ። ዲሲፒኤስ እነዚህን ጥያቄዎች ማሟላት ይችል አይችለ እንደሆነ የራሱ ግምትና ውሳኔ ሊሆን እንደሚችል እረዳለሁ።

**በጉልህ የተጻፈ ስም፤** ____________________________ **ፊርማ፤** __________________ **ቀን፤** __________

**ስልክ፤** ____________________ **ኢሜይል፤** ____________________________________

*መድልዎ አልባ ማስታወቂያ፣ በስቴት እና በፌድራላዊ ህገ ደንብ መሠረት፣ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ በእውን ወይንም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ወይንም በሚታሰብ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ ትዳር በመያዝም ሆነ ባለመያዝ፣ በመልክ፣ ለማፍቀር በሚፈልጉት የጾታ መደብ ዝንባሌ ምርጫ (sexual orientation)፣ ለመሆን በሚፈለግ የጾታ መደብ ወይንም የጾታዊነት ፍላጎት መገለጫ፣ (gender identity or expression)፣ በቤተሰብ የዝምድና አቋም (family status)፣ በቤተሰብ ኃላፊነት፣ በትምህርት ደረጃ፣ በፖለቲካ ዝንባሌ፣ በ ጄኔቲክ መረጃ, (genetic information)፣ በአንዳች እክል ምክንያት፣ በገቢ መንጭ፣ በቤተሰብ አባላት መካከል በሚፈጠር የእርስ በእርስ ግጭት ተጤቂ በመሆን፣ ወይንም በሚኖሩበት ቦታ ወይንም በሚሠሩት የሥራ ዐይነት የተነሣ፣ መድልዎ አያደርግም። ስለዚህ ጽሑፍ እና ተጨማሪ መረጃም ለማግኘት http://dcps.dc.gov/non-discrimination. ይቃኙ።*